# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**የከቲተ 05 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**- ወያኔ በፈጠረው ተንኮል ነዳጅ ጠፍቶ ሰነበተ፤**

**- ብሔራዊ የህዝብ አመጽ ሊነሳ ይችላል ብሎ ወያኔ ስጋት ገብቶታል፤**

**- በየክልሎች ውስጥ ዜጎች በርሀብ እና በምግብ እጥረት እየሞቱ መሆኑ ተጋለጠ፤**

የወያኔ ቡድን በፈጠረው ችግር ምክንያት በአዲስ አበባ እና በመላ ሀገሪቱ ከተሞች የነዳጅ እጥረት ተከስቶ ህዝቡ ሲታመስ ሰነበተ ፡፡

ሰው በላውና ዘረኛው የወያኔ ቡድን የሀገሪቱን ህዝቦች በርሀብ እና በድህነት እየቀጣ ለ20 ዓመታት ቢቆይም የሚፈጥራቸው ችግሮች ከግዜ ወደ ግዜ እየሰፉና እያደጉ ከመምጣታቸው በተጨማሪ መፍትሄ የማይገኝላቸው ደረጃ ላይ መድረሱ አሳሳቢ እና አደገኛ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ሰሞኑንም ወያኔ በፈጠረው ችግር ምክንያት በመላ ሀገሪቱ ነዳጅ ጠፍቶ የትራንስፖርት እጥረት ከመከሰቱም በተጨማሪ የእለት ጉርስ ማብሰያ የሆነው ጋዝ ጭምር በመጥፋቱ ህዝቡ ለከፋ ችግር ተዳርጎ የሰነበተ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ቤንዚን፤ ናፍታ እና የቤት ጋዝ በመጥፋቱ ገሚሱ በእግሩ ሌላው በመኪና የአዲስ አበባ ከተማ ነዳጅ ማደያዎችን እየዞሩ ቢጠይቁም አለ የሚል በመጥፋቱ መኪኖቻቸውን በመንገድ ዳር ጥለው ለመሄድ እንደተገደዱና ለቤት ፍጆታ ብለው የወጡትም ቢሆኑ ባዶ እጃቸውን በመግባታቸው ምግብ ማብሰያ እንደተቸገሩ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በህዝብ ስቃይ የሚደሰተው የወያኔ ቡድን የዓለም የነዳጅ ዋጋ እየቀነሰም ቢሆን በህዝቡ ላይ እየቆለለ መግዛት ከሚችለው በላይ እያሸከመው ለከፍተኛ ችግር ዳርጎት የነበረ ሲሆን አሁን ደግሞ የባሰውኑ ነዳጅ በየማጠራቀሚያ ዴፖዎች ውስጥ እያስቀመጠ ሆን ብሎ ህዝቡን በማሰቃየት ለችግር የዳረገው ከመሆኑም በተጨማሪ ገና ለገና የአለም ዋጋ ሊጨምር ይችላል በሚል አስቀድሞ ያስገባውን ነዳጅ በውድ ዋጋ ሊሸጥና ስንጥቅ ትርፍ ሊያግበሰብስ አስቦ እጥረቱ እንዲፈጠር ማድረጉ አሳዛኝ እና አሳፋሪ መሆኑ ታውቆዋል::

ከእሁድ ጥር 28 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በቂ የነዳጅ አቅርቦት ባለመኖሩ አዲስ አበባን ጨምሮ ሌሎች ከተሞችም በችግር ውስጥ የከረሙ ሲሆን በተለይ ብዙ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቶች ያሉባት ዋና መዲናዋ የነዳጅ እጥረቱ በመባባሱ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች ጭምር ለከፋ ችግር ተዳርገው ሲባዝኑ እንደሰነበቱ ለማየት ተችሎዋል::

ወያኔ በአጭር ግዜ ውስጥ ባደረገው የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ ከ7 ብር ተነስቶ ዛሬ የአንድ ሊትር ቤንዚን ዋጋ 16 ብር ከ45 ሳንቲም የአንድ ሊትር ናፍጣ ዋጋም 14 ብር እንዲሁም የአንድ ሊትር የቤት ጋዝ 12 ብር ከ36 ሳንቲም ሆኖ ባለበት ወቅት ከዚህ በላይ እንደገና ለመቀጠል ሰበብ እየፈለገ መሆኑ የሚያሳፍር እና የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ለህዝቡ ያለውን ጥላቻ አጉልቶ ያሳየበት መሆኑን አረጋግጦዋል::

ነዳጁን አስቀድሞ በዝቅተኛ ዋጋ አስገብቶ በዴፖ ውስጥ አስቀምጦ የነበረ ሲሆን ሰሞኑን በተለያዩ የአረብ ሀገራት የተነሳውን ብጥብጥ ተከትሎ የነዳጅ ዋጋ ሊያሻቅብ ይችላል በሚል ሰንካላ ምክንያት በርካሽ የተገዛውን በውድ ለመሸጥ አስቦ ለማደያዎች ባለመከፋፈሉ እጥረቱ ሊከሰት እንደቻለ ታውቆዋል::

ህዝቡን ፍጹም መናጢ ደሀ አድርገው ለስልጣናቸው ተገዥ ለማድረግ ሌት ተቀን እየሰሩ ያሉት የወያኔ ባለስልጣናት አሁንም በተፈጠረው ግርግር አሳብበው በነዳጅ ላይ ዋጋ ለመጨመር እቅድ እንዳላቸው የሚያመላክቱ ነገሮች እንዳሉም ለማወቅ ተችሎዋል::

በተፈጠረው የነዳጅ እጥረት ችግር ምክንያት ትራንስፖርት ጠፍቶ ህዝቡ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ ተቸግሮ ከመሰንበቱም በላይ ከነበረው ታሪፍ በተጨማሪ ከፍተኛ ሂሳብ እየከፈሉ ለመንቀሳቀስ ተገድደዋል::

ብዙዎቹ የመኪና ባለቤቶች ነዳጅ በመጥፋቱ መኪኖቻቸውን አቁመው በእግራቸው ከመንቀሳቀሳቸውም በላይ ወትሮም ትራንስፖርት እያንገላታው ያለውን ህዝብ ተቀላቅለው እንደገና ሌላ ተጨማሪ ትራንስፖርት ፈላጊ በመሆናቸው በችግር ላይ ችግር ተደራርቦ እንደነበር ታይቶዋል::

ለህዝቡ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ መኪኖችም በነዳጅ መጥፋት ምክንያት በውስጣቸው ያለውን ብቻ እስኪጨርሱ ድረስ ሰርተው ለመቆም እንደተገደዱ እና ህዝቡ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ሲሰቃይ እንደሰነበተ ተመልክቶዋል::

በተለይ እሁድ ምሽት እና ሰኞ ጠዋት በአዲስ አበባ በተለያዩ ማደያዎች ውስጥ ብጥብጥ ተነስቶ የነበረ ሲሆን አንዳንዶቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው በአደባባይ ወያኔን ሲያወግዙ ለማድመጥ ተችሎዋል። ባለ መኪኖች እና እግረኞች በጥምረት ባሰሙት ተቃውሞ የተደናገጠው የወያኔ ቡድን መትረየስ የጫኑ ፓትሮሎችን በከተማዋ በማሰማራት ጥብቅ ቁጥጥር ሲያደርግ እንደነበር እና አሁንም በስውር እና በግልጽ ጥበቃው ተጠናክሮ እንደቀጠለ ለማረጋገጥ ተችሎዋል።

በቱኒዚያና በግብጽ የታየው የህዝብ አመጽ በእኛም ሀገር በነዳጅ እጥረቱ ሳቢያ ሊነሳ ይችላል የሚል ስጋት ያደረበት የወያኔ ቡድን በፓትሮልና መሳሪያ በታጠቁ እግረኛ የፌዴራል ፖሊሶች ውጠራ እያደረገ ቢሆንም ህዝቡ በብስጭት አሁንም ብሶቱን በየቦታው ከመግለጽ አልተቆጠበም።ሁኔታውን የተከታተሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እንዳሉት ከሆነ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ከቀን ወደቀን እየገፋ ከመጣ ሌሎች ሀገር ያየነው አመጽ በእኛም ሀገር መከሰቱ አይቀሬ ነው ሲሉም ገልፀዋል።

ወያኔ በዓለም ላይ የነዳጅ እጥረት ቢከሰት በሚል ስጋት ለመከላከያ እና ለፌዴራል ፖሊስ መንቀሳቀሻ ብቻ እንዲሆን በማሰብ ነዳጅ በማጠራቀሚያ ዴፖዎች ውስጥ አሸጎ እያስቀመጠ በዜጎች ላይ አላስፈላጊ ጫና ከመፍጠሩም በተጨማሪ በኑሮ ውድነቱ ላይ ቤንዚን እያርከፈከፈ መገኘቱ አደገኛ አጣብቂኝ ውስጥ እየገባ መሆኑን እያመላከተ ነው ተብሎዋል።

በህዝብ ገንዘብ ከውጭ የሚመጡትን እቃዎች ግለሰቦች እንዲያስመጡ ተደርገው እንደገና ተመልሶ ለመንግስት ከእነዚሁ ግለሰቦች እየተገዛ ለህዝቡ በውድ ዋጋ እንዲሸጥ ሲደረግ የነበረ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ዛሬ የኑሮ ውድነቱ ህዝቡ መሸከም ከሚችለው በላይ ሲሆንበት እና መረረኝ በማለቱ ምንም ውስጥ ከወያኔ ጋር ንክኪ የሌላቸውን ነጋዴዎች እየተሳደበና ጥፋቱን ሊያላክክ ቢሞክርም ሳይሆንለት በመቅረቱ ስጋት የገባው እና አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀው ይሄው ቡድን መፍትሔ ብሎ የያዛቸው ነዳጅ አቅርቦትን መገደብ እና ሌሎች ነገሮችን ማድረጉ የችግሮች ማጠናከሪያ እንጂ መቅረፊያ እንዳልሆኑም ምንጮቹ አስረድተዋል።

በሰሞኑ የነዳጅ እጥረት ምክንያት ተቀማጭነቱ አዲስ አበባ የሆነ አንድ የአውሮፓ ሀገር ዲፕሎማት ተዘዋውሮ ማደያዎችን ከተመለከተ በሁዋላ ሲያጣ በብስጭት ለምን መለስ ዜናዊ ስልጣኑን አይለቅም ማስተዳደር አቅቶት በዋና መዲናዋ እንዲህ ያለ ችግር እስኪፈጠር መመልከት ወንጀል ነው ሲል በንዴት እና በብስጭት ሲያወግዝ እንደነበረም በቦታው ከነበሩ ሰዎች ማድመጥ ተችሎዋል።

በግብጽ የተደረገው የህዝብ ተቃውሞ ለፍሬ የበቃው በህብረት እና በአንድነት በመስራቱ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይባል አሁንም የወያኔን ቡድን ከስሩ ለመንቀል እራሱ በሰራቸው ስህተቶች እና በፈጸማቸው ወንጀሎች ላይ ተንተርሶ መረማመድ የሚቻለው አሁን እና አሁን ብቻ ነው ሲሉም አፅንኦት ሰጥተው ገልፀዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእለት ጉርስ መሸፈን እያቃተው ከገጠር ወደ ከተማ እየፈለሰ ያለውን አርሶ አደር ኢትዮጵያዊ ትርፍ አምራች አደረኩት እያለ እየለፈፈ የሚገኘው እብሪተኛው የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ለውርደት እንደተዳረገ ታወቀ።

ትርፍ አምራች ገበሬን ፈጥሬያለሁ..... ሚለየነር ገበሬ አፍርቻለሁ...... እድገት አስመዝግቤያለሁ እያለ ባለበት በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የከፋ ርሀብ ተከስቶ የድረሱልኝ ጥሪ ማሰማት መጀመሩ የዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችን እንዳስገረመ ታውቆዋል::

በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች ርሀብ እና የምግብ እጥረት የተከሰተ ሲሆን በተለይ በሱማሌና በኦሮሚያ ክልሎች ውስጥ በተከሰተው ርሀብ ምክንያት ዜጎች እንደቅጠል እየረገፉ እንደሚገኙ ታውቆዋል::

በሱማሌ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ብቻ ከ5 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ረሀብተኛ መኖሩ የተረጋገጠ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩት ህጻናት እና አሮጊቶች በየቀኑ እየሞቱ እንደሚገኙ ከክልሎቹ የደረሱን ጥቆማዎች አስረድተዋል::

ባዶ ጉራውን የሚነዛው ወያኔ ገበሬው የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ ባለበት በአሁኑ ሰዓት ትርፍ አምራች አድርጌዋለሁ እያለ የዓለም አቀፍ መንግስታትን ትኩረት ለመሳብ ቢሞክርም እያወራ ያለው ውሸት መሆኑ ሩቅ ሳይሄድ በአጭሩ እየተጋለጠ ሲሆን በአሁኑም ወቅት ያጋጠመው ተመሳሳይ እንደሆነ ታውቆዋል::

በርሀብ እና በምግብ እጥረት ምክንያት በብዙ መቶ የሚቆጠሩ ዘጎች እየረገፉ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ አንድም ዜጋ እንዳልሞተ አስመስሎ መደበቁ ያበሳጫቸው አንድ ስማቸው እንዲገለፅ ያልፈለጉ የእርዳታ ድርጅት ሰራተኛ ይሄንን አውቀን አስቀድመን ከሁለት ወር በፊት ጥሪ ብናቀርብም የእድገት እና ትራንስፎርሜሽኑ እቅድ ግቡን እንዳይመታ ለማድረግ ያደረጋችሁት ሴራ ነው ሲል በረከት ስምኦን መልስ ሰጥቶናል ሲሉ በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል::

ችግሩ አሁን እንደተከሰተና የምግብ እጥረት ብቻ እንደተፈጠረ አድርገው ጥሪ ማቅረባቸው ለዜጎች ህይወት ምንም ደንታ እንደሌላቸው የሚያመላክት ከመሆኑም በተጨማሪ እውነታው ግን ዜጎች አሁንም በየቀኑ እየሞቱ ለቀባሪ እያስቸገሩ ነው ሲሉ ሀዘን ባጠላበት ገጽታቸው ገልፀዋል::

ህዝብ በየቀኑ በርሀብ እየረገፈ ባለበት እና እራሱ ወያኔ የድረሱልኝ ጥሪ እያቀረበ ባለበት በዚህ ወቅት እድገት ያስመዘገቡ አርሶ አደሮች በሚል ሽልማት ሲሰጥ መሰንበቱ ሌላው የወያኔ ቁርጦ ቀጥል ድራማ መሆኑ ተጋልጦዋል::

ሐሙስ ጥር 26 ቀን 2003 ዓ.ም የምግብ እጥረት በመከሰቱ እርዳታ ስጡኝ ብሎ ጥሪ ባቀረበ በሶስተኛው ቀን እሁድ ዕለት ጥር 29 ቀን 2003 ዓ.ም በአዳማ(ናዝሬት) ትርፍ አምራች ገበሬዎች በሚል ሽልማት ሲሰጥ መዋሉ ህዝቡን አስገርሞዋል::

ረሀብ በሀገሪቱ ነግሶ ህይወት እያጠፋ በግልጽ እየታየ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት ተብሎ ህዝብን ለማታለል እየተሰራ ያለው አሳፋሪ ድራማ እነ መለስ ዜናዊ እንደ እምቡዋይ ካብ እየገነቡ ያሉት የውሸት ስራም በደቂቃ እየተጋለጠ ተንዶ እያሳፈራቸው ቢሆንም በሀገር እና በህዝብ ሀብት እና ገንዘብ ግን ያለ አንዳች ሀፍረት አሁንም ፕሮፓጋንዳ መንዛታቸው እጅግ አስገራሚ ነው ተብሎዋል::

ዛሬ በየገጠሩ በሚኖሩት አርሶ አደሮች ላይ በሚጣልባቸው ከፍተኛ ግብር የተነሳ መክፈል እያቃታቸው ቀዬአቸውን ጥለው እየተሰደዱ ሲሆን አንዳንዶቹም እስከ ዕለተ ሞቲ ድረስ ቀዬን ጥዬ አልሄድም በማለት የእርሻ በሬዎቻቸውን እየሸጡ ለወያኔ እየሰጡ ባዶ እጃቸውን ቀርተው የሚላስ የሚቀመስ አጥተው በርሀብ እያለቁ መሆኑን የጠቆሙት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት በመላ ሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች የምግብ እጥረቱና ርሀቡ እጅግ ከመስፋፋቱም በላይ አስጊ ደረጃ ላይ መድረሱም ታውቆዋል፡፡

በአማራ ቆላማና በረሀማው ክፍል ውስጥ አፋር እና ትግራይ እንዲሁም ቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ብሎም ደቡብ ክልል ውስጥ ዜጎች ለከፍተኛ ርሀብ ተጋልጠው የሚገኙ ሲሆን ለስርዓቱ ተገዥ እና አጎብዳጅ የሆኑትን ጥቂቶቹን ብቻ እየመረጠ ትርፍ አምራች አደርጌያቸዋለሁ ብሎ ባዶ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ ቢሆንም ያለው ተጨባጭ ሀቅ ግን አሁንም ገበሬው በከፋ ችግር ውስጥ መኖሩን ነው ሲሉ ምንጮቹ አስረድተዋል፡፡

ብቸኛ አስመጪ አከፋፋይ እና ሻጭ ሆኖ ብቻውን እየሰራ የንግድ ማዕከሎቹን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ የበላይነቱን በያዘበት በአሁኑ ሰዓት የአንድ ኩንታል ማዳበሪያ ዋጋ ከ1500 ብር በላይ እየሸጠ ገበሬውን እየዘረፈ የሚገኘው ወያኔ አሁንም በርሀቡ ህዝቡን እየቀጣ መሆኑ ታውቆዋል፡፡